## መዘክር

### ግፍአሙ

<< የእግዚአብሄር ዳኝነት የእግዚአብሄር
እውነት
የሚጠበቅበት የድሆች መብት፣
እጅና እግሩን ታስሮ በግፍ ሰንሰለት
ያለአንድ ጠበቃ ያለአንድ ረዳት
ፍርድ ለመቀበል ቀርቦ ፍርድ ቤት፣
በቀማኞችና በሌቦች ችሎት
ይሙት በቃ ብለው ሁሉም በአንድነት
ያመጽ ፍርድ ፈርደው ገደለው
ሲቀብሩት።

ይህን ግፍ አየና አበጀ አስተውሎ
በጦር እንደወጉት ልቡ ባዘን ቆስሎ፣
መንፈሱ በቁጣ እንደ እሳት ተቃጥሎ
የእውነትን ደመኞች ለመበቀል ብሎ
ወረደ በረሃ ቤት ንብረቱን ጥሎ።

ዳኞች ዳኝነትን ከቀበሩት ገድለው
የእግዜርን አደራ እምነቱን አጉድለው፣
የሰጠናቸውን ስልጣን ተከልለው
እኛኑ ሲያጠቁን ጠባቂዎች መስለው፣
መቀማት ሲመርጡ መጠበቁን ጥለው
ካሾች እኛ ስንሆን እነሱ በድለው፣
አርደው ሲጨርሱን አንድ ባንድ
አናጥለው
እንደ ቡዋዘዘ ከብት ጠባቂ እንደሌለው፣
ለመብት ሲከላከል ሊሞት እንደማለው
እንደ ቆራጡ ወንድ እንዳበጀ በለው፣
እኛስ ለመብታችን የማንታገለው
ከጅልነት በቀር ምን ምክንያት አለው።

የመብትን ፋና ያርነትን ጮራ
የሚለይበትን ሰው ከእንስሳ ተራ፣
ከፍ አድርጎ ይዞ ሲሄድ እያበራ
በነሴ በረሃ በጎንቻ ተራራ፣
ግፈኞች ከበውት ከቀኝ ከግራ
ቀን ከሌት ሲያድኑት ወንጀል እንደሰራ፣
ለምቾቱ አያስብ ለህይወቱ አይፈራ
እንደ አምላክ ስለሰው ሲቀበል መከራ፣
መሄዳችን ላይቀር ነገ ስንጠራ
ወደማንቀርበት ወደ ሙታን ስፍራ፣
የበሉትን ቀጥቶ የጊዜን አደራ
የማይቀረውን ሞት መሞት ከሱ ጋራ
የሚያጸድቅ ነበር ወዲያው የሚያኮራ። >>

ከሃዲስ አለማየሁ/ ፍቅር እስከመቃብር